DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# በ FERPA ሥር የመብት ማሳወቂያ

## (Notification of Rights under FERPA)

የ ቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶችና የግል ጉዳይ የመከበር ድንጋጌ (The Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) ለወላጆችና እድሜአቸው 18 ዓመት እና ከዚያም በላይ ለሆኑ ተማሪዎች ("ብቁ የሆኑ ተማሪዎች")፤ የተማሪዎችን የትምህርት መረጃዎች በሚመለከት የተወሰኑ መብቶችን ያጎናጽፋል። ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ መረጃውን ይፋ ማድረጉ ለተማሪው ምዝገባ ወይንም ዝውውር አገልግሎት ተግባር የሚውል እስከሆነ ድረስ፣ ዲሲፒኤስ ለሌላ ትምህርት ቤት ወይንም በትምህርት ቤት ዲስትሪክቱ ተማሪው ሊመዘገብ ለሚፈልግበት ወይህን መመዝገብ ለሚያስብበት፣ ወይንም አስቀድሞ ተመዝግቦ ለሚገኝበት ትምህርት ቤት የትምህርት መረጃዎችን ያለ ስምምነት ይፋ ሊያወጣ ይችላል።

**(1)** ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ (DCPS) መረጃዎችን እንዲሰጥ ጥያቄዎች በቀረቡለት በ 45 ቀናት ውስጥ የተማሪውን የትምህርት **መረጃዎች የመመርመርና የማጣራት መብት።** ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ለመመርመር የሚፈልጉትን መረጃ(ዎች) በመጥቀስ ለትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህር ጥያቄዎቹን በጽሑፍ ማቅረብ አለባቸው። የትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህርም ሆነ ወይም አግባብ ያለው ሌላ የትምህርት ቤት ባለሥልጣን መረጃው የሚገኝ በትን ሁኔታ ዎች በማመቻቸት፣ መረጃዎቹ ሊመራመሩና ሊታዩ የሚችሉበትን ጊዜና ቦታ በመጥቀስ ለወላጆችም ሆነ ወይም ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች ያስታው ቃል።

**(2)** ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ በ FERPA የተማሪው ግላዊ መብቶች ሥር፣ የተማሪው የትምህርት መረጃዎች፣ ትክክል አይደለም፣ ያሳስታል፣ ተዛብ ቷል፣ ተዛንፏል ብለው የሚያምኑበትን፣ **እንዲቃና፣ እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት።** ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ትክክል አይደለም፣ ተዛንፏል፣ ተሳስ ቷል፣ አለበለዚያም ግላዊ መብቱን ይጻረራል ብለው የሚያምኑበት የተማሪው የትምህርት መረጃዎች ለምን ተስተካክሎ መቅረብ እንደሚገባው በመግለጽ ተስተካክሎ እንዲ ቀርብ ዲሲፒኤስን በጽሑፍ መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን፣ ከተሳሳተው መረጃ ውስጥ የትኛው ክፍል እንዲስተካከልና እንዲቃና እንደሚፈልጉ፣ እንዲሁም ለምን ትክክል ሊሆን እንዳልቻለ እና ለምንስ መለወጥ እንደሚያስፈልገው ጭምር በግልጽ በመጥቀስ ለትምህርት ቤታቸው ርእሠ መምህር ችግሩን ማቅረብና ማመልከት ይችላሉ። በጥያቄውም መሠረት፣ ዲሲፒኤስ የተሳሳተውን መረጃ ለማስተካከል የማይፈልግ ሆኖ ከተገኘ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ስለ ደረሰበት ውሳኔ ለወላጅ ወይም ብቁ ሆኖ ለሚገኘው ተማሪ በማስታ ወቅ መረጃውን ማቃናት ለሚያስችል አቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ እንደሚችሉ ማሳወቅ አለበት። ወላጅ ወይም ብቁ ሆኖ የሚገኝ ተማሪ፣ ጉዳያቸው በችሎት እንዲታይላ ቸው የማድረግ መብት ያላቸው መሆኑ በሚገለጽላቸው ሰዓት፣ ስለ ችሎቱ ሂደት ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

**(3)** ያለ ማንም ስምምነት FERPA የተማሪው መረጃዎች ይፋ እንዲወጡ ማዘዝ ከሚቻልበት የሥልጣን ደረጃ በስተቀር፣ በተማሪው የትምህርት ማኅደር ውስጥ የሚገኙ **ግላዊነትን የሚያመለክቱ መለያ መረጃዎች ሁሉ ይፋ እንዲወጡ (በጽሁፍ) የመስማማት መብት።** ለምሳሌ FERPA፣ ዲሲፒኤስ ትምህርት ነክ ስለሆኑ ጉዳዮች ሕጋዊ ዝን ባሌና ፍልጎት ይኖራቸዋል ብሎ ለሚያምንባቸው የትምህርት ቤት ባለሥልጣናት መረጃዎችን ያለፈቃድ ስምምነት እንዲያገኙ ሥልጣን ይሰጣል። የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ማለት፣ በዲሲፒኤስ፣ የተቀጠረ አስተዳዳሪ፣ ሱፐርቫይዘር፣ መምህር ወይም ድጋፍ ሰጪ የትምህርት ቤት አባል (የጤና ወይም የሕክምና ቡድን አባል እና የሕግ አስከባሪዎች ቡድን አባላትን የመሰሉትን ጨምሮ)፣ ልዩ ተግባራትን (ለምሳሌ ያህል እንደ ጠበቃ፣ ኦዲተር ሰሚ ኮሚቴ፣ የሕክምና አማካሪ ወይም ፈውስ ሰጪ (thera-pist) የመሳሰሉትን) ልዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ዲሲፒኤስ የተኮናተራቸው፤ ወይም ተማሪው እንዲመዘገብ በሚሻበት፣ ወይንም ለወደፊት ለመመዝገብ በሚያስብበት የሌላ ትምህርት ቤት ባለሥልጣን፣ ወይም ተማሪው በአሁኑ ሰዓት ተመዝግቦ በሚገኝበት ትምህርት ቤት፣ ወይንም ወላጅ፣ ተማሪ ወይንም እንደ የሥነሥርዓት ወይንም አቤቱታ ሰሚ በመሳሰሉ ኦፊሽያል በሆኑ ኮሚቴ ውስጥ ወይንም የሌላ የትምህርት ባለሥልጣን ሥራውን በአግባቡ ማከናወን እንዲችል ወይንም እንድትችል ለመርዳት በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግል ሰው ነው። የትምህርት ቤት ባለሥልጣን፣ ሙያዊ የኃላፊነት ተግባሩን ለመወጣት እንዲችል ወይም እንድትችል የትምህርት ማስረጃዎችን መመር መር ከፈለገ ወይም ከፈለገች ሕጋዊ ትምህርታዊ ዝንባሌ ይኖረዋል ወይም ይኖራታል ማለት ነው።

**(4)** **የመረጃዎችን ጥንቅር ይፋ እንዳይወጣ የማድረግ መብት።** ደንቡ በሚፈቅደው፣ ባለው መብት እና በራሱ ሥልጣን በመጠቀም፣ ዲሲፒኤስ ያለ ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ስምምነት፣ አብዛኛውን ጊዜ ጉዳት የማያስከትሉ ወይም የግል መብትን የማይጻረሩ ተብለው የሚገመቱ መሠረታዊ "የመረጃዎች ጥንቅር" ("directory information") በዲስትሪክቱ ሕግ ጥላ ሥር እና በ FERPA አማካይነት፣ ያለ ወላጆች ስምምነት ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ፈቃድ መረጃዎችን ይፋ ማድረግ ይችላል። የመረጃዎች ጥንቅሩም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ሀ. የተማሪው ስም
- ለ. የተማሪው አድራሻ
- ሐ. የተማሪው የተመዘገበ የስልክ ቁጥር
- መ. የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም
- ሰ. በኦፊሲየል ዕውቅ በሆኑ ክንዋኔዎችና ስፖርቶች መሳተፍ
- ረ. የአትሌቲክ ቡድኖች አባላት ክብደትና ቁመት
- ሠ. ተማሪው የተቀዳጃቸው ዲፕሎማዎች እና ሽልማቶች
- ሽ. ተማሪው የተወለደበት ዘመንና የትውልድ ቦታ
- ቀ. ቀድሞ የተማረበት ትምህርት ቤት ስም
- በ. ትምህርት ገበታ ላይ የተገኘባቸው ቀናት

**ወላጅ ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ከላይ** ተመልክተው **የቀረቡትን** መረጃዎች **(i) ተያይዞ የሚገኘውን "የተማሪ መረጃዎችን ይፋ ማድረጊያ** ("**Release of Student Directory Information**") **ቅጾችን አጠናቆ መሙላት የሚያስፈልግ ሲሆን በተጨማሪም በ www.dcps.dc.gov/enroll ላይ ወይንም በክልል ትምህርት ቤትዎ መመዝገብ ይቻላል።**

**(5)** ዲሲፒኤስ FERPA ተሟልተው እንዲገኙ የሚጠብቃቸውን ጉዳዮች ለማሟላት ያለመቻልን በሚመለከት፣ ለዩኤስ የትምህርት መምሪያ **አቤቱታ የማቅረብ መብት።** FERPA ን ሕገ ደንብ የሚመራው ድርጅት ጽሕፈት ቤት ስምና አድራሻ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Ave. SW, Washington, DC 20202 ነው።